


# حقوق المرأة

## في الإسلام

# የሴቶች መብት በኢስላም

(أمهري)

**በአላህ** ስም እጅግ በጣም ርኅሩኅ

በጣም አዛኝ በሆነው፡፡

# የሴት ማዕረግ በእስልምና

የመጀመርያ እትም

- ርዕስ፡ የሴት ማዕረግ በእስልምና
- ደራሲ፡- ዶ/ር ጀማል በደዊ
- የአማርኛ እትም 1 (2010)
- የመጀመርያ እትም 1 (2010)
- ትርጉም፡- ወሂብ አብዱልዋሲዕ ኩርቱ
- የንድፍ ዝግጅት፡-IIPH ሪያድ- ሳኡዲ አረቢያ
- የፊልም ስራና የሽፋን ንድፍ፡- ሳሞ የህትመት ግሩፕ

# የሴት ማዕረግ በእስልምና

## የመጀመርያ እትም

## حقوق المرأة في الاسلام

ዶ/ር ጀማል በደዊ

ትርጉም
ወሂብ አብዱልዋሲዕ ኩርቱ

الدار العالمية للكتاب الاسلامي
አለም አቀፍ ኢስላማዊ መፅሐፍት አሳታሚ ድርጅት

የህትመት ባለቤትነት መብት © 2010 አለም አቀፍ ኢስላማዊ መፅሐፍት አሳታሚ ድርጅት
በንጉሥ ፈሃድ ብሔራዊ ቤተ መፃህፍት የህትመት መረጃ መዝገብ የሰፈረ

በደዊ ጀማል
የሴት ማዕረግ በእስልምና፡፡ ዶ/ር ጀማል በደዊ
ሪያድ፡2010

45 ገፅ ፤ 21 ሳ.ሜ

RDMK ጠንካራ ሽፋን፡ 978-603-501-071-9

1- የሴት ማዕረግ በእስልምና    I- ወሂብ አብዱልዋሲዕ ኩርቱ(ተርጓሚ)
II - ርዕስ

219.1 ዲዋይ    1431/2049

ህጋዊ ተቀማጭ ገንዘብ ቁጥር፡1431/2049
RDMK ጠንካራ ሽፋን፡ 978-603-501-071-9

የአሳታሚው ሙሉ መብት የተጠበቀ ሲሆን ያለ አሳታሚው የፅሁፍ ፈቃድ የዚህን መፅሐፍ አንድም ክፍል በማንኛውም ሁኔታ ማባዛት፣ማስተላለፍ፣ በኤሌክትሮኒክስ ወይም በሜካኒካል መንገድ፣ በፎቶ ኮፒ ፣'እስካን' ማድረግ፣ በቀረፃ፣ ወይም በተለያዩ የኢንተርኔት መረጃ መለዋወጫ ዘዴዎች ማሰራጨት ወይም በማንኛውም የመረጃ ማከማቻ እና መልሶ ማግኛ ስርዐት ተጠቅሞ ማስተላለፍ ከህግ ውጭና በህግ የሚያስቀጣል ነው፡፡
ስለዚህ እባኮን በኤሌክትሮኒክ መዝገብ የታተሙትን ይግዙ፡፡ከዚያ ውጭ ባለ ህገወጥ የኤልክትሮኒክ ቅጅ ከመጠቀም አይተባበሩ፡፡ ለዚህ ምግባሮ ከወዲሁ እናመሰግኖታለን፡፡

አለም አቀፍ ኢስላማዊ መፅሐፍት አሳታሚ ድርጅት(IIPH)
የመ.ሣ.ቁ.55195 ሪያድ 11534 ሳዑዲ አረቢያ
ስልክ፡ 966 1 4650818/4647213- Fax:966 1 4633489
ኢ-ሜይል:iiph@iiph.com.sa- iiphsa@gmail.com
www.iiph.com.sa

| ተራ ቁ. | ማውጫ | ገፅ |
| --- | --- | --- |
| 1 | የአሳታሚው ማስታወሻ | |
| 2 | መግቢያ | |
| 3 | ከታሪክ ማህደር | 11 |
| 4 | ሴቶች በጥንት ሥልጣኔዎች | 12 |
| 5 | ሴቶች በእስልምና | 20 |
| 5.1 | መንፈሳዊ ህይወትን በተመለከተ | 22 |
| 5.2 | ማህበራዊ ህይወትን በተመለከተ<br>( ሀ )ከልጅነት እስከ እውቀት | 28 |
| | (ለ)የትዳርን ህይወት በተመለከተ | 30 |
| | (መ) የእናት ማዕረግ | 36 |
| 5.3 | ሴትና የኢኮኖሚ ድርሻዋ | 39 |
| 5.4 | የፖለቲካ ተሳትፎን በተመለከተ | 42 |
| 6 | ማጠቃለያ | 46 |

## የአሳታሚው ማስታወሻ

ምስጋና ይግባው ለአላህ ሰውን ካንዲት ነፍስ ፈጥሮ ጥንድ ላደረገው! እንዲሁም ዝግ ልቦችን በዋህይ(በአላህ ራእይ) ለከፈቱ፣ የታወሩ አይኖችን በእውቀት ላበሩ፣ ደንቆሮ ጆሮችን ጥበብን እንዲሰሙ ላደረጉት ነቢዩ ሙሀመድ፣የአላህ እዝነትና ሰላም ይስፈንባቸው፡፡

በማከልም የወንዶች አጋር የሆኑት ሴቶች ማዕረጋቸው ሁሌ ጥያቄ ላይ የወደቀ ቢመስልም እስልምና በዚህ አጭር የጥናት ፅሁፍ ምን ያህል ደረጃዋን እንደጠበቀ ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡የሃሊፋክሱ ምሁር ዶ/ጀማል በደዊ የእስምናን አቋም ሚዛን ባለው መልኩ ሴት በህብረተሰብ ውስጥ ያላትን መብትና ግዴታ ትናንትና ዛሬ ምን እንደሚመስል ለማስቀመጥ ሞክረዋል፡፡

በእምነት ፣ በማህበራዊ ፣ በኢኮኖሚያዊ ፣ እንዲሁም በፖለቲካው የህይወት መስክ የእስልምና መርሃ ህይወት ለጠያቂ የሚገባውን ከቁርአንና ከነቢዩ(ሰለላሁ ዓለሂ ወሰለም) ህይወት ብሎም ከሶሃባ ተግባራዊ ህይወት በመነሳት መልስ ተሰጥቶበታል፡፡

በእርግጥም ውድ አንባቢ በዚህ አጭር የጥናት ፅሁፍ መጨረሻ የአላህ (ሱ .ወ)የተሟላ ፀጋ የሆነው እስልምና ሁሉንም ፍጡር (ሴቱንም ወንዱንም) የሚያጠቃልል የህይወት መርህ እንደሆነ መረዳት እንዳስቻለህ ተስፋ እናደርጋለን ።

መሐመድ አብዱልሙህሲን አ ቱዌጅሪ
አለም አቀፍ የእስላማዊ ህትመት ድርጅት(IIPH)
ሪያድ- ሳዉዲ ዐረቢያ
1430ሂጅሪያ
2009እ.አ.አ

# መግቢያ

ሴቶች በህብረተሰብ ውስጥ ያላቸው ማዕረግ አዲስም ጉዳይ ያልሆነና መልስ ያላገኘም ነው።

በዚህም ጉዳይ ላይ ምዕራባያዊያን አንባቢያን የእስልምናን አቋም በስፋትና በጥልቀት ያልተመለከቱትና አላማውን ያልተረዱት ጉዳይ ነው።

በዚህ የጥናት ፅሁፍ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ የእስልምናን አቋም በአጭርና እውነትን በመመርኮዝ ማብራሪያ ተሰጥቶበታል። የእስልምና መመሪያ የሆኑትን ቁርዐንና የነቢዩ ሙሐመድ/ሰ.ዓ.ወ/ ንግግሮችና ክንውኖች ማለትም «ሃዲስ እና ሱና» መሠረት በማድረግ በትክክልና በማያዳላ ሁኔታ የእስልምናን ገፅ በእውነተኛ አቋምና አመለካከት ተገልጿል።

ይህ የጥናት ወረቀት በመጀመሪያ በቅድመ እስልምና የነበረውን የሴት ሁኔታ በአጭሩ ያብራራል። በመቀጠልም ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ጥያቄዎች ላይ ትኩረት ያደርጋል።

በህብረተሰብ ውስጥ ሴት ያላት ማዕረግ ላይ የእስልምና አቋም ምንድ ነው?

«ከዘመኑ መንፈስ ጋር» የእስልምና አቋም ምን ያህል ይመሳሰላል ወይም ይለያያል?

በተጨማሪ እስልምና እንደገና በተረጋገጠበት ሰዓት የትኛው አቋም ነው በሰፊው የሰፈነው? በቅርብ አስርት አመታት ተገኘ የተባለውን «የሴት መብት» እንዴት እናወዳድራለን? የሚሉ ይገኙበታል።

# ከታሪክ ማህደር

ከላይ እንደተገለፀው የዚህ ፅሁፍ ዋናው አላማ እስልምና የሴትን ክብርና መብት እንደገና ለመጠበቅ ያደረገው አስተዋፅኦ /ወይም ማድረግ ያልቻለውን/ አስተዋፅኦ አድልኦ በሌለበት ሁኔታ ለመገመትና ለመረዳት ነው:: ይህንንም አላማ ከግብ ለማድረስ ከእስልምና በፊት /610 ምዕተ አመት/[1] የነበሩትን የቀድሞ ስልጣኔዎችና ሃይማኖቶች በአጠቃላይ ሴቶችን እንዴት እንደሚመለከቱ በአጭሩ ማገናዘብ ጠቃሚ ይሆናል:: ሆኖም እዚህ ላይ ስለ ሴት ሁኔታ የሚገልፀው የጥናት ፅሁፍ የሚያወሳው እስከ አስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ማትም ከእስልምና በኋላ አስራ ሁለት ክፍለ ዘመን ነው::

---

[1] የዚህ ፅሁፍ የአመት አቆጣጠር የአውሮፓውያን ይሆናል::

## ሴቶች በጥንት ሥልጣኔዎች

ኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ የህንድ ሴትን ማዕረግ ሲገልፅ፡-

« ዋናው የህንድ መመሪያ ሴት በወንድ መታዘዝ ነው:: "ማኑ" እንደሚለው ሴቶች ሌት ተቀን በመከታዎቻቸው ስር በጥገኝነት ይኖራሉ:: የውርስ ህግ አያውቃቸውም፤ የውርሰ ንብረት ሴቶችን ሳያጠቃልል በወንዶች ብቻ ይከፋፈላል::»[2]

በሂንዱ ፅሁፎች ውስጥ የጥሩ ሚስት መግለጫ እንደሚከተለው ተቀመጧል:- «አዕምሮዋ፣ ንግግሯና ሰውነቷ በወንዱ የተገዛች የሆነችና በዚህም አለም በሚቀጥለውም አለም ከፍተኛ ዝና ትጎናፀፋለች፤ ከባሏ ጋርም አንድ ቤት ይኖራታል::»[3]

የአቴናውያን ሴቶች ከህንዳዊያን ወይም ከሮማዊያን የተሻሉ አይደሉም:-

---

[2] The Enyclopedia Britannica 11th ed., 1911, Vol. 28, P.782.
[3] In Mace, David and Vera, Marriage East & west, Dolphin Books, Double day and Co., Inc…, N. Y… 1960

«የአቴናዊያን ሴቶች ሁሌ ዝቅተኛ፣ ለአንዳንድ ወንዶች ማለትም ለአባቶቻቸው ለወንድሞቻቸውና ለሌሎች ወንድ ለሆኑ ዘመዶቻቸው ተገዢ ነበሩ::»[4]

ትዳርን በተመለከተ የርሷ መስማማት በአጠቃላይ አስፈላጊ አልነበረም::

«የቤተሰቧ ፍላጎቶችግዴታ የሚሆንባትናየሚያመጡላት ባል የርሷ ጌታ ሲሆን ለርሷም እንግዳ ቢሆንም መቀበል አለባት::»[5]

በታሪክ አዋቂዎች የሮማዊያን ሚስት እንዲህ ተገልፃለች:: «ምንም የማታውቅ፣ ዝቅተኛ፣ ታዳጊ ልጅ፣ በራሷ ፍላጎት ምንም መስራት ወይም ማቀድ የማትችልና በሷ ሁሌ የርሷ ሃላፊና ጠባቂ ሲሆን በባሏ ስርም የምትኖር ናት::»[6]

በሮማውያን የስልጣኔ ጊዜ የነበረው የሴቶች ህጋዊ ማዕረግ ከኢንሳይክሎፒዲያ ብሪታኒካ እንዲህ ይነበባል:- በሮማዊያን ህግ በታሪካዊ ጊዜያቶችም ወቅት ሴት በሙሉ ጥገኛ ነበረች:: ስታገባ እርሷና ንብረቷ ወደ ባሏ ይዛወራል.....ሚስት ባል የሚገዛትንብረት ነበረች::ማለትም ባርያ ለጥቅም ብቻ እንደሚገዛ ትገዛ ነበር:: ሴት አንድም

---

[4] Allen, E.A, History of Civilization, Vol.3,P.444.
[5] Ibid P.443:
[6] Ibid, P. 550:

የመንግስት ወይም የህዝብ ቢሮ ውስጥ መስራት አትችልም...... ምስክር፣ ዋስ፣ አስተማሪ ወይም የሙዝየም(ቤተ መዘክር) ሃላፊ መሆን አትችልም:: የሰው ልጅ ማሳደግ ወይም እርሷ ራሷ በጉዲፈቻ ማደግ ወይም ኑዛዜ ማድረግ ወይም ውል መዋዋል አትችልም::»[7]

የእስካንዲኔቪያን ሴቶች ስንመለከት :-

> «ቢያገቡም፣ ባያገቡም፣ ያለማቋረጥ በሃላፊያቸው ስር ይኖራሉ:: እስከ አስራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ማለትም የክርስቲያን ህገመንግስት መጨረሻ ይሰራበት የነበረው ህግ አንድ ሴት ያለ ሃላፊዋ ፈቃድ ብታገባ ሃላፊዋ ከፈለገ በህይወት እስካለች ድረስ ንብረቷን ማስተዳደር ይችላል::»[8]

የእንግሊዛዊያንን ህግ ስንመለከት:-

> «..... በጋብቻ ወቅት ሚስት የነበራት ማንኛ ውም ንብረት የባሏ ይሆናል:: በጋራ በሚመሩት ኑሯቸው ወቅት መሬትን

---

[7] The Encyclopedia Britannica, 11th ed., 1911, op.cit. Vol. 28, P.782.
[8] Ibid., P.783.

ማከራየትና የእርስት ንብረት ትርፍ ላይ
ሃላፊ ባል ነበር:: ጊዜያቶችም አልፈው
የእንግሊዝ ፍርድ ቤቶች ያለ ሚስት ፈቃድ
ንብረት ወደ ባል እንዳይዛወር መመሪያ
አረቀቁ:: ሆኖም ባል ንብረትን
እንዲቆጣጠር፣ ምርትን፣ትርፍ ገንዘብ
እንዲቀበል መብቱ እንደተጠበቀለት
ነበር:: የሚስትን ንብረት በተመለከተ የባል
ተፅዕኖ ፍፁም ነበር:: እንዳስፈለገው
ቢያወጣ መብት ነበረው::»[9]

በአስራ አራተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ነበር ሁኔታው መቀየር የጀመረው::

«በተደጋጋሚ የወጡት ህጎች:- የመጀመሪያው የ1870 ያገቡ ሴቶች ንብረት ህግ፣ የ1882ና የ1887 በማሻሻል የወጡ ህጎች እንደ ሴተላጤዎች(ያላገቡ ሴቶች)፣ ባል የሞተባቸው፣ ፈት ሴቶች ሁሉ ያላገቡ ሴቶችም ውል እንዲያደርጉ የሚል መብት ተቀዳጁ::»[10]

---

[9] Encyclopedia Americana International (Edition), vol.29.P.108
[10] Encylopedia Britannica, 1968, Vol. 23, P.624.

እስከ አስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ የጥንታዊ ህግ አዋቂ የነበረው ሰር ሄንሪ ማይን እንዲህ ሲል ፅፏል:- «የክርስቲያን ድርጅቶችን ማንኛውም ሃሳብ የማይጠብቅ ህብረተሰብ ካለ ያገቡ ሴቶች የግል መብት ያረጋገጠላቸውን የመካከለኛውን የሮማዊያንን ህግ የሚመስል ነው።»[11]

ጆን እስቲዎርት «ዘ ሳብጀክሽን ኦፍ ውሜን» በሚለው ፅሁፍ:-

«ስልጣኔና ክርስትና የሴትን ፍትሃዊ መብቷን የመለሱ ተደርገው ነበር ተደጋግሞ የተነገረን። ግን ሴት ትክክለኛ የባል አገልጋይ ... ህጋዊ ግዴታዋ እስካሁን ድረስ በተለምዶ ባሪያዎች ከሚባሉት አትለይም።»[12]

የቁርዐን ትዕዛዞች የሴትን ማዕረግ ወይም ደረጃን በተመለከተ ያስፈሩትን ከማየታችን በፊት ከመፅሐፍ ቅዱስ ትዕዛዞች በጥቂቱ ብንመለከት ጉዳዩን በበለጠ ግልፅ ያደርገዋል። ይህም ለማያዳላ ግምገማ ጥሩ መሠረት ይሰጣል።

በሙሴ ህግ ስለሚስት የሰፈረውን ኢንሳይክሎፒዲያ ባይብሊካ ሲገልፅ:- «አንድ ሰው ሚስት ሲያጭ ማለት

---

[11] Quoted in Mace, Marriage East and West, Op. cit, P.81
[12] Ibid., PP. 82-83

በቀላሉ እርሷን በገንዘብ ክፍያ ማግኘት ማለት ነው::»[13] ከህግ አንፃር ሲመለከቱት ለትዳሯ ሕጋዊነት የሴቷ መስማማት አስፈላጊ አልነበረም:: «የሴቷ መስማማት ያለአስፈላጊ ነው፤ የርሷ ለጋብቻ ፍቃደኛ መሆን አለመሆን በህግ ላይ አልተገለፀም::»[14]

እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ሙስሊሙ በሚያምንበት በቀደምት ከተረጋገጡት /ሐይማኖቶች/ እምነቶችና የመጀመሪያው ጽሁፋቸው ጋር አሁን ካሉት ሐይማኖታዊ ድርጅቶች አሰራር ጋር በእርግጥ የማይጣጣም ነው::

የፍችን መብት በተመለከተ በኢንሳይክሎፒዲያ ባይብሊካ ይህን እናነባለን:- «ሴቷ የወንዱ ንብረት እንደመሆኗ መጠን እርሱ እርሷን እንደፈለገ የመፍታት መብት አለው::[15] ለመፍታት ሙሉ መብት ያለው ባል ብቻ ነበር:: «ከሙሴ ህግ ፍቺ የወንድ ብቻ ልዩ መብት ነበር......»[16]

የቤተክርስቲያንም አቋም እስከ ቅርብ ክፍለ ዘመን ድረስ በሙሴ ህግና በጊዜው የበላይነት በነበራቸው ባህሎችና የሐሳብ አመለካከት ተፅዕኖ ነበረባት::

---

[13] Encyclopedia Biblica, 1902, Vol.3, P.2942.
[14] ibid., P. 2942.
[15] Ibid., P.2947
[16] The Encyclopedia Britannica, 11th ed., op.cit., P.782.

ዴቪድ ቬራሚክ "ሚሬጅ ኢስት ኤንድ ዌስት" በሚለው መፅሐፋቸው የሚከተለውን ፅፈዋል፡-

«የወረስነው የክርስትና እምነታችን ፍርዶችን ከማጎደል ነፃ ነው ብሎ የሚገምት የለም። በቀድሞ የቤተክርስቲያን አባዎች አነስታይ ጾታን በዝቅተኛነት የገለፁ ፅሁፎች ተመሳሳይ ማግኘት አዳጋች ይሆናል። የታወቀው የታሪክ ምሁር ሌኪ እንደተናገረው /አባዎች ከፃፏቸው በጣም ያልተለመዱ በጣም እንግዳ ችግሮች ሁሉ ሴት የሃጢአት ሁሉ እናት እንደሆነች ትቆጠር ነበር። ሴት በመሆኗ ልታፍርበት ይገባታል። በዚህ አለም ላይ ባመጣችው እርግማን ያለ ንስሐ በቅጣት ያለማቋረጥ መኖር አለባት። በልብሷ ማፌር አለባት፤ ምክንያቱም የእርሷ መውደቅ መታሰቢያ ነው። በተለይ በውበቷ ማፌር አለባት፤ ምክንያቱም ዋናው የሰይጣን መሳሪያ ነውና/። ሌላው በሴት ላይ የተደረገው በጣም ፀያፍ ንግግር የቴርተሊያው ነው፡- " እናንተ ሴቶች ታውቃላችሁ እያንዳንዳችሁ ሴት መሆናችሁን? እግዚያብሔር በዚህ ፆታ ላይ የፈረደው ፍርድ ጥፋቱ አሁንም በዚህ ፆታና ኑሮ ውስጥ ያለ ነው። እናንተ የሰይጣን በሮች ናችሁ። የተከለከለውን የዛፍ ፍሬ

በመብላት ለመጀመሪያ ጊዜ ፈጣሪን የከዳችሁ እናንተ ናችሁ። አዳምን በማሳመን ጉብዝና በሌለው ሰይጣን እንዲጠቃ ያደረጋችሁ እናንተ ናችሁ። የእግዚያብሄርን ምስል ሰው በቀላሉ ያጠፋችሁ።

በእናንተ ሰበብ የእግዚያብሄር ልጅ እንዲሞት ተደረገ።" ቤተክርስቲያን ሴቶችን በዚህ ሁኔታ በዝቅተኝነት ብቻ ሳይሆን የምትመለከተው ከዚህ በፊት ሴት የነበራትን ህጋዊ መብቷንም ጭምር ነበር የከለከለቻት።»[17]

[17] Mace, Marriage East and west, Op. cit, PP. 80-81,

# ሴቶች በእስልምና

አለም የድንቁርና ጥቁር መጋረጃ ባካበባት ዘመን መካከል ለሰው ልጅ የሚያገለግል አዲስ የሚደነቅና ሁለንተናዊ የፈጣሪ መመሪያ በሰፊው የአረቢያ በረሃ አስተጋባ:-

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ ٱتَّقُوا۟ رَبَّكُمُ ٱلَّذِى خَلَقَكُم مِّن نَّفْسٍ وَٰحِدَةٍ وَخَلَقَ مِنْهَا زَوْجَهَا وَبَثَّ مِنْهُمَا رِجَالًا كَثِيرًا وَنِسَآءً وَٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ ٱلَّذِى تَسَآءَلُونَ بِهِۦ وَٱلْأَرْحَامَ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ عَلَيْكُمْ رَقِيبًا (١)

« እናንተ ሰዎች ሆይ! ያንን ከአንዲት ነፍስ: /ከአዳም/ የፈጠራችሁን ከርስዋም መቀናጆዋን /ሔዋንን/ የፈጠረው ከነርሱም ብዙ ወንዶችንና ሴቶችን የበተነውን ጌታችሁን ፍሩ::ያንንም በርሱ የምትጠያየቁበትን አላህንና ዝምድናዎችንም (ከመቁረጥ) ተጠንቀቁ አላህ በእናንተ ላይ ተጠባባቂ ነውና::::» /4:1/

አንድ ምሁር ይህን የቁርዐን ጥቅስ አስመልክቶ እንዳሰፈረው:- « እንደሚታመነው የሴትን ሰብአዊ ፍጡርነት በሁሉም አቅጣጫ እንዲህ በሚያስደንቅ

አጭር አገላለፅ ጥልቅና አዲስነት ባለው ጥበብ የተሞላበት የፈጣሪ ህግና ማሳመኛ በማንኛውም ፅሁፍ በአሮጌውም በአዲሱም የለም።» [18]

ይህን ቅዱሳዊ እና ተፈጥሯዊ ፅንሰሃሳብ ቁርዓን አበክሮ ሲገልፅ የሚከተለውን አስፍሯል፡-

هُوَ ٱلَّذِى خَلَقَكُم مِّن نَّفْسٍ وَٰحِدَةٍ وَجَعَلَ مِنْهَا زَوْجَهَا لِيَسْكُنَ إِلَيْهَا «እርሱ ያ ከአንዲት ነፍስ /ከአዳም/ ፈጠራችሁ ከርሷም መቀናጆዋን ወደ እርሷ ይረካ ዘንድ ያደረገ ነው..............» /7:189/

فَاطِرُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۚ جَعَلَ لَكُم مِّنْ أَنفُسِكُمْ أَزْوَٰجًا «ሰማያትንና ምድርን ፈጣሪ ነው ከነፍሶቻችሁ ሴቶችን......) /42:11/

وَٱللَّهُ جَعَلَ لَكُم مِّنْ أَنفُسِكُمْ أَزْوَٰجًا وَجَعَلَ لَكُم مِّنْ أَزْوَٰجِكُم بَنِينَ وَحَفَدَةً وَرَزَقَكُم مِّنَ ٱلطَّيِّبَٰتِ ۚ أَفَبِٱلْبَٰطِلِ

---

[18] El-khouly, Al Bahly, 'min usus kadiyat Almar'ah' (Al-wa'ay-Islam, ministry of wakf, Kuwait, Vol.3, No.27, June 9,1965), P.17.

يُؤْمِنُونَ وَبِنِعْمَتِ ٱللَّهِ هُمْ يَكْفُرُونَ (٧٢)«አላህም ከነፍሶቻችሁ /ከጉሶቻችሁ/ ለናንተ ሚስቶችን አደረገ ለናንተም ከሚስቶቻችሁ ወንዶች ልጆችን የልጅ ልጆችንም አደረገላችሁ ከመልካሞችም ጸጋዎች ሰጣችሁ ታዲያ በውሸት /በጣዖት/ ያምናሉን?»/16:72/

የቀረው የዚህ ጥናት ፅሁፍ ሴት በህብረተሰብ ውስጥ እስልምና ያረጋገጠላትን ማዕረግ ማለትም በመንፈሳዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፓለቲካዊ መስክ የሚመለከት ይሆናል::

1. መንፈሳዊ ህይወትን በተመለከተ

የሴቶች መብቶችንና ግዴታችምን በተመለከተ በአላህ ዘንድ ከወዶች ጋር በእኩል ደረጃ እንደሚታዩ በቁርዐን ውስጥ በማያሻማ ሁኔታ ተገልጿል:-

كُلُّ نَفْسٍ بِمَا كَسَبَتْ رَهِينَةٌ (٣٨)

«ነፍስ ሁሉ በሠራችው ስራ ተያዥ ናት» /74:38/

فَٱسْتَجَابَ لَهُمْ رَبُّهُمْ أَنِّى لَآ أُضِيعُ عَمَلَ عَٰمِلٍ

مِّنكُم مِّن ذَكَرٍ أَوْ أُنثَىٰ ۖ بَعْضُكُم مِّنۢ

بَعْضٍ«ጌታቸውም እኔ ከናንተ ከወንድ ወይም ከሴት የሰራን ስራ አላጠፋም፤ ከፊላችሁ ከከፊሉ ነው በማለት ለነርሱ ልመናቸውን ተቀበለ፡፡» /3:195/

مَنْ عَمِلَ صَٰلِحًا مِّن ذَكَرٍ أَوْ أُنثَىٰ وَهُوَ

مُؤْمِنٌ فَلَنُحْيِيَنَّهُۥ حَيَوٰةً طَيِّبَةً ۖ وَلَنَجْزِيَنَّهُمْ

أَجْرَهُم بِأَحْسَنِ مَا كَانُوا۟ يَعْمَلُونَ (٩٧)

« ከወንድ ወይም ከሴት እርሱ አማኝ ኾኖ በጎን የሰራ መልካም ኑሮን በእርግጥ እናኖረዋለን፤ ይሰሩትም ከነበሩበት ነገር በመልካሙ ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን::» /16:97/

وَمَن يَعْمَلْ مِنَ ٱلصَّـٰلِحَـٰتِ مِن ذَكَرٍ أَوْ
أُنثَىٰ وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَأُو۟لَـٰٓئِكَ يَدْخُلُونَ ٱلْجَنَّةَ
ولا يُظْلَمُونَ نَقِيرًا (١٢٤)

«ከወንድ ወይም ከሴት እርሱ አማኝ ሆኖ ከበጎ ስራዎች አንዳችን የሚሰራም ሰው እነዚያ ገነትን ይገባሉ፤ በተምር ፍሬ ላይ ያለችን ነጥብ ያክል እንኳ አይበደሉም::» /4:124/

በቁርዓን መሰረት በአደም የመጀመሪያ ስህተት ሴት አትወቀስም:: ሁለቱም አላህን ባለመታዘዛቸው ስህተተኛ እንደነበሩ፣ ሁለቱም ይቅርታ እንደጠየቁና አላህም እንደማራቸው በቁርዓን ተጠቅሷል::

فَأَزَلَّهُمَا ٱلشَّيْطَـٰنُ عَنْهَا فَأَخْرَجَهُمَا مِمَّا كَانَا فِيهِ

«ከርሷም ሰይጣን እንዳስወገዳቸው ከውስጡም ከነበሩት /ድሎት/ አወጣቸው»/2:36/

فَوَسْوَسَ لَهُمَا ٱلشَّيْطَـٰنُ لِيُبْدِىَ لَهُمَا مَا وُۥرِىَ عَنْهُمَا
مِن سَوْءَٰتِهِمَا وَقَالَ مَا نَهَىٰكُمَا رَبُّكُمَا عَنْ هَـٰذِهِ ٱلشَّجَرَةِ

إلا أن تَكُونَا مَلَكَيْنِ أَوْ تَكُونَا مِنَ ٱلْخَـٰلِدِينَ (٢٠)
وَقَاسَمَهُمَآ إِنِّى لَكُمَا لَمِنَ ٱلنَّـٰصِحِينَ (٢١) فَدَلَّـٰهُمَا
بِغُرُورٍ ۚ فَلَمَّا ذَاقَا ٱلشَّجَرَةَ بَدَتْ لَهُمَا سَوْءَٰتُهُمَا وَطَفِقَا
يَخْصِفَانِ عَلَيْهِمَا مِن وَرَقِ ٱلْجَنَّةِ ۖ وَنَادَىٰهُمَا رَبُّهُمَآ أَلَمْ
أَنْهَكُمَا عَن تِلْكُمَا ٱلشَّجَرَةِ وَأَقُل لَّكُمَآ إِنَّ ٱلشَّيْطَـٰنَ لَكُمَا
عَدُوٌّ مُّبِينٌ (٢٢) قَالَا رَبَّنَا ظَلَمْنَآ أَنفُسَنَا وَإِن لَّمْ تَغْفِرْ
لَنَا وَتَرْحَمْنَا لَنَكُونَنَّ مِنَ ٱلْخَـٰسِرِينَ (٢٣) قَالَ ٱهْبِطُوا۟
بَعْضُكُمْ لِبَعْضٍ عَدُوٌّ ۖ وَلَكُمْ فِى ٱلْأَرْضِ مُسْتَقَرٌّ وَمَتَـٰعٌ
إِلَىٰ حِينٍ (٢٤)

«ሰይጣንም ከዕፍረተ ገላቸው የተሸሸገውን ለነርሱ ሊገልፅባቸው በድብቅ ንግግር ጎተጎታቸው፤ ጌታችሁም መልአኮች እንዳትሆኑ ወይም ከዘላለም ነዋሪዎች እንዳትሆኑ እንጂ ከዚች ዛፍ አልከለከላችሁም አላቸው:: እኔ ለናንተ በእርግጥ ከሚመክሩዋችሁ ነኝ ሲልም ማለላቸው:: በማታለልም አዋረዳቸው ከዛፊቱም በቀመሱ ጊዜ ዕፍረተ ገላቸው ለሁለቱም ተገለጠችላቸው ከገነት ቅጠልም በላያቸው ላይ ይደርቱ ጀመር፡፡ ጌታቸውም ከዚች ዛፍ አልከለከልኋችሁምን? ሰይጣንም ለናንተ ግልፅ ጠላት ነው አላልኳችሁምን? ሲል ጠራቸው::

«ጌታችን ሆይ! ነፍሶቻችንን በደልን ለኛ ባትምር ባታዝንልንም በእርግጥ ከከሳሪዎቹ እንሆናለን አሉ:: /አላህ/ ከፊላችሁ ለከፊሉ ጠላት ሲሆን ውረዱ ለናንተም በምድር ላይ እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ መርጊያና መጠቀሚያ አላችሁ አላቸው:: /7:20-24/

ከዚህም በተጨማሪ በአንድ የቁርዓን ጥቅስ አዳም በተለይ እንደተወቀሰ ይገልፃል:-

فَأَكَلَا مِنْهَا فَبَدَتْ لَهُمَا سَوْءَٰتُهُمَا وَطَفِقَا يَخْصِفَانِ عَلَيْهِمَا مِن وَرَقِ ٱلْجَنَّةِ وَعَصَىٰٓ ءَادَمُ رَبَّهُۥ فَغَوَىٰ (١٢١)

«ከርሷም በሉ ለነርሱም ሃፍረተ ገላቸው ተገለፀች:- ከገነትም ቅጠል በላያቸው ላይ ይለጥፉ ጀመር:: አደምም የጌታውን ትዕዛዝ /ረስቶ/ ጣሰ /ከፈለገው መዘውተር/ ተሳሳተም::» /20:121/

ሃይማኖታዊ ግዴታዎችን ስናወሳ ማለት እንደ ሶላት፣ ጾም፣ ዘካ ወይም የድሐ ምፅዋትን መክፈልና ሐጅ መሄድን በተመለከተ ሴት ከወንድ በምንም አትለይም:: በአላህ ባለው እዝነት በእርግጥ በአንዳንድ ሁኔታዎች ምክንያት ሴት ያለባትን መንፈሳዊ ግዴታ ከማከናወን

ትታቀባለች። ለምሳሌ ያህል ሴት በወር አበባዋ ጊዜ ፣ልጅ ከወለደች እስከ አርባ ቀን ድረስ ሶላት ከመስገድና ጾም ከመጾም ነፃ ያደርጋታል። በእርግዝናዋ ጊዜ በልጇና በራሷ ላይ አደጋ የሚያመጣ መስሎ ከታያት ከመጾም እንደምትታቀብ ተገልጿል። ከላይ በተገለፁት ችግሮች ሳቢያ ሶላት ቢያልፋት ግን ለማሟላት ግዴታ የለባትም። ምንም እንኳን ሴቶች በነቢዩ ጊዜ ወደ መስጊድ የሚሄዱ ቢሆንም በተለይ በአርብ ቀን በሚደረገው ፀሎት ስብሰባ ላይ እንደ ወንድ የመገኘት ግዴታ የለባቸውም።

እነዚህ ግልፅና ገርነትን ያካተቱ የእስልምና መመሪያዎች ናቸው። ምክንያቱም በርህራሄ ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው ነው። ለምሳሌ ልጇን በምጠባበትና በምትንከባከብበት ወቅትም በሶላት ሰዓት መስጊድ የመሄድ ግዴታ የለባትም። እነዚህ መመሪያዎች የርሷን የአካልና የስነልቦና ለውጦች፣ ያላትን ተፈጥሯዊ የሴት ባህርይ ግምት ውስጥ በማስገባት የተደነገጉ ናቸው።

## 2. ማህበራዊ ህይወትን በተመለከተ

### ሀ. ከልጅነት እስከ እውቀት

በአረቢያ ጉሳዎች ዘንድ ማህበራዊ ተቀባይነት ያገኘ የነበረውን ህፃን ሴትን መግደል ቁርዓን እንደሌላው ማንኛውም የግድያ ወንጀል በመቁጠር ይህንን ልምድ ከለከለ::

وَإِذَا ٱلْمَوْءُۥدَةُ سُئِلَتْ (٨) بِأَىِّ ذَنۢبٍ قُتِلَتْ (٩)

«በህይወቷ የተቀበረችውም ሴት ልጅ በተጠየቀች ጊዜ በምን ወንጀል እንደተገደለች»/81:8-9/

ሴት ልጆቻቸውን በጥላቻ አይን የሚመለከቱትን አላህ በቁርዓን እንዲህ ሲል ይቃወማል:-

وَإِذَا بُشِّرَ أَحَدُهُم بِٱلْأُنثَىٰ ظَلَّ وَجْهُهُۥ مُسْوَدًّا وَهُوَ كَظِيمٌ (٥٨) يَتَوَٰرَىٰ مِنَ ٱلْقَوْمِ مِن سُوٓءِ مَا بُشِّرَ بِهِۦٓ ۚ أَيُمْسِكُهُۥ عَلَىٰ هُونٍ أَمْ يَدُسُّهُۥ فِى ٱلتُّرَابِ ۗ أَلَا سَآءَ مَا يَحْكُمُونَ (٥٩)

«አንዳቸውም በሴት ልጅ በተበሰረ ጊዜ እርሱ የተቆጨ ሆኖ ፊቱ ጠቁሮ ይውላል:: በርሱ ከተበሰረበት ነገር መጥፎነት በውርደት ላይ ሆኖ ይያዘውን? ወይስ በአፈር

ውስጥ ይደብቀውን? /በማለት እያምታታ / ከሰዎች ይደበቃል፤ ንቁ የሚፈርዱት /ፍርድ/ ምንኛ ከፋ!»
/16:58-59/

እስልምና የሴት ልጅን ህይወት ከመጠበቅ ባሻገር ለወደፊቱ የህይወቷ ዘመን ፍትህ እንዳይጓደልባትና በዝቅተኛነት እንዳይመለከቷት ከማድረጉም በላይ በርህራሄና በፍትህ እንድትኖር የነቢዩ ሙሐመድ/ሰ.ዓ.ወ/ ንግግር ያስገነዝበናል:-
«ማንኛውም ሴት ልጅ ያለው ሰው በህይወት እያለች ያልቀበራት ፤ያላዋረዳት፣ በርሷም ላይ ወንድ ልጁን አብልጦ ያልተመለከተ አላህ ገነትን ይመነዳዋል::»/የኢብን ሐምበል የሀዲስ መፅሐፍ ቁ.1957/
«ለአቅመ አዳም ብቁ እስከ ሆኑ ድረስ ሁለት ሴት ልጆችን አንከባክቦ ያሳደገ እኔና እርሱ በፍርድ ቀን አንድ ላይ እንመጣለን በማለት /ሁለት ጣቶቻቸውን በማገናኘት/ አረጋገጠዋል::»
በተመሳሳይ ሁኔታም ሁለት እህቶቹን የሚል የነቢዩ ሙሐመድ/ሰ.ዓ.ወ/ ንግግር /በኢብን ሐምበል `የሀዲስ መፅሐፍ ቁ.2104/ ይገኛል::

እውቀትንም የማግኘትና የመማር መብትም ሴቶች የሚለዩበት ምንም ምክንያት እንደሌለ ነቢዩ ሙሐመድ/ሰ.ዓ.ወ/ አረጋግጠዋል::« እውቀትን መፈለግ የማንኛውም ሙስሊም ግዴታ ነው::» እዚህ ላይ ሙስሊም ሲባል ሴቶችንም ወንዶችንም ያጠቃልላል::[19]

ለ. የትዳርን ህይወት በተመለከተ

ቁርዐን በትክክል እንዳስቀመጠው ትዳር ማለት ሁለት የህብረተሰብ ክፍሎች የሚጋሩትና አላማውም ሰብአዊ ፍጡርን ከማፍራቱም በላይ መንፈሳዊንና አካላዊ ደህንነትን በማጣመር የሚረጋግጥ ነው:: መሰረቱም ፍቅርና ርህራሄ ነው::

ትዳርን በተመለከተ ስሜትን በጣም ከሚማርኩ የቁርዐን ጥቅሶች ውስጥ ይህ ይገበኝታል:-

وَمِنْ ءَايَـٰتِهِۦٓ أَنْ خَلَقَ لَكُم مِّنْ أَنفُسِكُمْ أَزْوَٰجًا لِّتَسْكُنُوٓا۟ إِلَيْهَا وَجَعَلَ بَيْنَكُم مَّوَدَّةً وَرَحْمَةً ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَـَٔايَـٰتٍ لِّقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ (٢١)

«ለናንተም ከነፍሶቻችሁ /ከጎሶቻችሁ/ ሚስቶችን ወደ ነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ በመካከላችሁም ፍቅርና እዝነትን ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው በዚህ

[19] በአንዳንድ እርግጠኛ ፅሁፎች ላይ ወንድንም ሴትንም ይጨምራል ይላል:: ሆኖም ቃሉ ሌላ ትርጉም እስካልተሰጠው ድረስ በአጠቃላይ ሰላማዊ ግዴታ በእኩል ወንድንም ሴትንም የሚመለከት ነው::

ውስጥ ለሚያስተውሉ ሕዝቦች ታምራቶች አሉ፡፡»
/30:21/

የእስልምና ሕግ ሴቶችን ያለፈቃዳቸው መዳር እንደማይቻል ያዛል፡፡ በዚህም መሠረት በኢብን አባስ እንደተወራው ነቢዩ ሙሐመድ/ሰ.ዓ.ወ/ ዘንድ አንዲት ልጃገረድ በመምጣት አባቷ ያለርሷ ፈቃድ ሲድራት እንዳስገደዳት ገለፀች፡፡ ግን የአላህ መልክተኛ እንደትመርጥ ድል ሰጧት....../ትዳሩን መቀበል ወይም ያለመቀበል/፡፡ /ኢብን ሐንበል ቁ.2469/፡፡ በሌላ አገላለፅ ልጅቷም፡- «በእርግጥ ትዳሩን ተቀብያለሁ ግን ሴቶች እንዲያውቁ የፈለግኩት ቤተሰብ/በሃይል መዳር/ መብት እንደሌለው ነው» አለች ይባላል፡፡
/ኢብን ማጃህ ቁ.1873/

በትዳር ወቅት የሚደረግላት ማንኛውም አስተዋፅኦ በተጨማሪ 'መኸር' ማለትም በጋብቻ ውል ላይ የሚሰፍር የጋብቻ ስጦታዋ ሙሉ መብት እንዳላት በተለይ ተዟል፡፡ይህ የግል ንብረቷ የሆነና ወደ አባቷ ወይም ወደ ባሏ የማይዛወር ነው፡፡ በእስልምና የምንገነዘበው 'መኸር'(ጥሎሽ) ወይም የጋብቻ ስጦታ በአንዳንድ ባህል

እንደሚደረገው ለሴት የሚከፈል የገንዘብ ዋጋ ሳይሆን ፍቅርና ውዴታን የሚገልፅ የስጦታ ምልክት ነው።

የትዳር ህጎች በእስልምና ግልፅ የሆኑና ከቀጥተኛ የሰው ልጅ ተፈጥሮ ጋር ተቆራኝተው የሚሄዱ ናቸው። የወንድንም፣ የሴትንም አካላዊና ስነልቦናዊ አፈጣጠር ከግምት ውስጥ በማስገባት ከሃላፊነት በስተቀር እኩል መብት እንዳላቸው ይገልፃል። ይህም በማንኛውም የጋራ ኑሮ የተለመደና በሰው ተፈጥሮ ውስጥም የሚዘልቅ ነው። ቁርዓንም ይህን ሲገልፅ:-

وَلَهُنَّ مِثْلُ ٱلَّذِى عَلَيْهِنَّ بِٱلْمَعْرُوفِ ۚ وَلِلرِّجَالِ عَلَيْهِنَّ دَرَجَةٌ ۗ وَٱللَّهُ عَزِيزٌ حَكِيمٌ (٢٢٨) «ለነርሱም /ለሴቶች/ የዚያ በነርሱ ላይ ያለባቸው /ግዳጅ/ ብጤ በመልካም አኑዋኑዋር /በባሎቻቸው ላይ መብት/ አላቸው ለወንዶችም ጣጣቸውን ስለሚሸከሙ /በነሱ ላይ ብልጫ አላቸው።» (2:228)

ይህ መበላለጥ የሚገልፀው «ቀዋሙን»የሚለውን የቁርዓን ቃል ሲሆን አያያዝንና የህይወት ጥበቃን ያጠቃልላል። ይህም የሚያሳየን በተፈጥሮ የፆታ ልዩነት መኖሩንና ደካማዋ ፆታ ጥበቃ

እንደሚያስፈልጋት ነው:: ይሁን እንጂ ወንድ ቤተሰቡን በሃላፊነት ይመራል ማለት ባል በሚስት ላይ አምባገነን ነው ማለት አይደለም:: እስልምና ቤተሰብን በተመለከተ ለሚደረጉ ውሳኔዎች በጋራ መመካከርንና መስማማትን አበክሮ ይገልፃል:: ቁርዓንም የሚከተለውን አስፍሯል:-

فَإِنْ أَرَادَا فِصَالًا عَن تَرَاضٍ مِّنْهُمَا وَتَشَاوُرٍ فَلَا جُنَاحَ عَلَيْهِمَا

«....../ወላጆቹ/ ከሁለቱም በሆነ መዋደድና መመካከር /ልጁን ከጡት/ መነጠል ቢፈልጉ በሁለቱም ላይ ሃጢአት የለባቸውም» /2:233/

ከዚህም በተጨማሪ የሚስት መሰረታዊ መብቷ በቁርዓን ትኩረት የተሰጠበትና ነቢዩ ሙሐመድም/ሰ.ዓ.ወ/ ትህትና የባልንጀርነት ስሜት በተሞላበት መንፈስ እንዲንከባከቧቸው አዟል:: ቁርዓንም ይህን በተመለከተ ሲገልፅ:-

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ لَا يَحِلُّ لَكُمْ أَن تَرِثُوا۟ ٱلنِّسَآءَ كَرْهًا ۖ وَلَا تَعْضُلُوهُنَّ لِتَذْهَبُوا۟ بِبَعْضِ مَآ ءَاتَيْتُمُوهُنَّ إِلَّآ أَن يَأْتِينَ بِفَـٰحِشَةٍ مُّبَيِّنَةٍ ۚ وَعَاشِرُوهُنَّ بِٱلْمَعْرُوفِ ۚ فَإِن

كَرِهْتُمُوهُنَّ فَعَسَىٰٓ أَن تَكْرَهُوا۟ شَيْـًٔا وَيَجْعَلَ ٱللَّهُ فِيهِ خَيْرًا كَثِيرًا (١٩)

«.......በመልካምም ተኗኗሯቸው ብትጠሏቸውም / ታገሡ/ አንዳችን ነገር ልትጠሉ አላህም በርሱ ብዙ ደግ ነገርን ሊያደርግ ይችላልና::» /4:19/

ነቢዩሙሐመድ/ሰ.ዓ.ወ/ እንደተናገሩት:- «ከእናንተ ምርጥ ማለት ለቤተሰቡ ምርጥ የሆነው ነው:: እናም ለቤተሰቤ ምርጥ በመሆኔ ከናንተም ሁሉ ምርጥ ነኝ::»

ጥሩ አማኞች በፀባያቸው ምርጥ የሆኑና ለሚስቶቻቸው ምርጥ የሆኑ ናቸው::» /ኢብን ሐንበል ቁ.7396/

በዚህም መሠረት በዚያን ጊዜ ሚስቶቻቸውን የሚያሰቃዩ መጥፎ ባሎች እንደነበሩና ለቤተሰቦቻቸውም ጥሩ እንዳልሆኑ በነቢዩ ሚስቶች ተነግሯል::

ትዳሯን በተመለከተ ሴት ያላት የመወሰን መብት ተረጋግጧል:: በዚህም አኳያ እርምጃው ያላማረን ትዳር ከወዲሁ መጨረሻውን መሻት ወይም በፍቺ የመገላገል መብት እንዳላት ታውቋል:: ሆኖም የቤተሰብን ህልውና ለመጠበቅ ሲባል በጊዜያዊ ስሜት በመገፋፋትና የችኮላ ውሳኔ ከመወሰን ለማቀብ ፍቺን ለሚሹ ወንዶችና

ሴቶች አንዳንድ እርምጃዎችን እዲወስዱና የተወሰኑ ጊዜዎችን እንዲጠብቁ ይደረጋል::
በተፈጥሮ የሴቶችን አንፃራዊ ስሜታዊነትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለፍቺ የሚያደርሱ አሳማኝ ምክንያቶችን ለዳኛ ማቅረብ አስፈላጊ ነው:: ሆኖም በጋብቻ ውል ውስጥ ከሰፈረ እንደ ወንድ እሷም የፍርድ ቤትን እርዳታ ሳትጠይቅ ባሏን መፍታት ትችላለች::

ትዳርና ፍቺን በሚመለከት የእስልምና ህግ የሆኑትን አመለካከቶች ቸል የማይባሉና በተናጠል መታየት የሚገባቸው ጉዳዮች ናቸው::

ግን የትዳር ግንኙነትን መቀጠል የማይቻልበት ማገኛውም ምክንያት ሲያጋጥም ወንዶች መጨረሻው ለጋስ ወይም ርህራሄ የተሞላበት እንዲሆን ጥረት እንዲያደርጉ ቁርዓን ያስተምራል:-

وَإِذَا طَلَّقْتُمُ ٱلنِّسَاءَ فَبَلَغْنَ أَجَلَهُنَّ فَأَمْسِكُوهُنَّ بِمَعْرُوفٍ أَوْ سَرِّحُوهُنَّ بِمَعْرُوفٍ ۚ وَلَا تُمْسِكُوهُنَّ ضِرَارًا لِّتَعْتَدُوا ۚ

«ሴቶችን በፈታችሁና /በዒዳ/ ጊዜያቸውን በደረሱ ጊዜ በመልካም ያዙዋቸው/ተማለሷቸው/ ወይም በመልካም ሁኔታ አሰናብቷቸው፤ ለመጎዳትም ወሰን ታልፉባቸው ዘንድ አትያዙዋቸው» /2:231/

ٱلطَّلَٰقُ مَرَّتَانِۖ فَإِمۡسَاكُۢ بِمَعۡرُوفٍ أَوۡ تَسۡرِيحُۢ بِإِحۡسَٰنٖۗ

«ፍቺ ሁለት ጊዜ /ከዚህ በኋላ/ በመልካም መያዝ ወይም በበጎ አኳኋን ማሰናበት ነው.........»/2:229/

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِذَا نَكَحۡتُمُ ٱلۡمُؤۡمِنَٰتِ ثُمَّ طَلَّقۡتُمُوهُنَّ مِن قَبۡلِ أَن تَمَسُّوهُنَّ فَمَا لَكُمۡ عَلَيۡهِنَّ مِنۡ عِدَّةٖ تَعۡتَدُّونَهَاۖ فَمَتِّعُوهُنَّ وَسَرِّحُوهُنَّ سَرَاحٗا جَمِيلٗا (٤٩)

« እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ምእምናንን ባገባችሁና ከዚያም ሳትነኩዋቸው በፊት ከፈታችኋቸው ጊዜ ለናንተ በነሱ ላይ የምትቆጥሩዋት ዒዳ/የሶስት ወር ደም ጥራት ወይም ሶስት ወር መታገስ/ ምንም የላችሁም አጠቃሟቸውም/ ጉርሻ ስጡዋቸው መልካም መሰናበትንም አሰናብቷቸው።» /33:49/

**መ. የእናት ማዕረግ**

አላህን ከመገዛት ቀጥሎ ለወላጅ ትሁት መሆንን እስልምና አበክሮ ያሳስባል።

وَوَصَّيْنَا ٱلْإِنسَـٰنَ بِوَٰلِدَيْهِ حَمَلَتْهُ أُمُّهُۥ وَهْنًا عَلَىٰ وَهْنٍ

«ሰውንም በወላጆቹ /በጎ እንዲያደርግ/ በጥብቅ አዘዝ ነው ። እናቱ ከድካም በላይ በሆነ ድካም አረገዘችው።» /31:14/

وَوَصَّيْنَا ٱلْإِنسَـٰنَ بِوَٰلِدَيْهِ إِحْسَـٰنًا حَمَلَتْهُ أُمُّهُۥ كُرْهًا

وَوَضَعَتْهُ كُرْهًا وَحَمْلُهُۥ «ሰውንም በወላጆቹ በጎ መዋልን በጥብቅ አዘዝነው ። እናቱ በችግር ላይ ሆና አረገዘችው በችግርም ወለደችው......» /46:15/

وَوَصَّيْنَا ٱلْإِنسَـٰنَ بِوَٰلِدَيْهِ حُسْنًا ... (٨)

«ሰውንም በወላጆቹ መልካም አድራጎትን አዘዝነው......./29:8/

ከዚህ በተጨማሪ እናቶችን በጥሩ ሁኔታ መያዝን ቁርዓን አበክሮ ይገልፃል፦

﴿وَقَضَىٰ رَبُّكَ أَلَّا تَعْبُدُوٓا۟ إِلَّآ إِيَّاهُ وَبِٱلْوَٰلِدَيْنِ إِحْسَـٰنًا﴾«ጌታህም/ እንዲህ ሲል/ አዘዘ ። እርሱን እንጂ ሌላን አትገዙ በወላጆቻችሁም መልካምን ስሩ.......»/17:23/

አንድ ሰው ወደ ነቢዩ ሙሐመድ/ሰ.ዓ.ወ/ ዘንድ መጥቶ «ከሰዎች ሁሉ ለኔ ምርጥ ጓደኛዬ ማን ነው?» ብሎ ጠየቃቸው ነቢዩም(ሰ.ዓ.ወ) እናትህ ብለው መለሱለት» ሰውየውም ከርሷ ሌላ ብሎ ጠየቀ «ነቢዩም» « እናትህ ብለው መለሱ» እንደገና «ከርሷ ሌላ ብሎ ጠየቀ» ነቢዩም « እናትህ በማለት መለሱ እንደገና ለመጨረሻ ጊዜም ጠይቃቸው እርሳቸውም «አባትህ ብለው» መከሩት። /በአልቡካሪና ሙስሊም የተዘገበ ነቢዩ ሃዲስ/
ሌላው የነቢዩ ምርጥ ንግግር «ገነት በእናቶች እግር ስር ናት» ብለዋል። /አል ኒሳኢ ኢብን ማጃህ አህመድ የተዘገቡ የነቢዩ ሃዲሶች ይገልፃሉ/
«ለሴቶች ጥሩ የሆነው /በፀባዩ/ ፀጋ ሲሆን ክፉ የሚባለው ደግሞ እነርሱን የሚሰድብ ነው።»

### 3. ሴትና የኢኮኖሚ ድርሻዋ

ሴት ከእስልምና በፊትና በኋላ / እስከ አለንበት ክፍለ ዘመን/[20] የተከለከለችውን የግል ንብረት ባለቤትነት መብት በእስልምና ተረጋግጧል:: በእስልምና ህግ ውስጥ ሴት የራሷ እርስት ወይም የገንዘብ ሃብት ባለቤትነት የተረጋገጠ ነው:: ይህም መብት ከማግባቷ በፊትም ካገባች በኋላ ለውጥ አያመጣም:: ንብቷን በከፊል ሆነ በአጠቃላይ ለመግዛት ፣ለመሸጥ ወይም ለማስያዝ ሙሉ መብት አላት:: ሴት ስለሆነች ብቻ ዝቅተኛ ነች የሚል የሰፈረ ህግ የለም:: እዚህ ላይ መጠቀሰ ያለበት እንዲህ ያለው መብት ከጋብቻ በፊትና ከዚያም በኋላ የምታገኘውን ንብረት ያጠቃልላል::

የስራ መቀጠርን መብት በተመለከተ በእስልምና ውስጥ መታወቅ ያለበት ነገር ቢኖር በህብረተሰብ ውስጥ ያላት

---

[20] ለምሳሌ በፈረንሳይ ህግ ውስጥ ሴቶች ውል እንዲዋዋሉ የሚያዝ ህግ እስከ 1938 ድረስ አልተሻሻለም ነበር:: አሁንም ቢሆን ያገባች ሴት የግል ንብረቷን እንድትጠቀም፡፡ የባሏ ሙሉ ፈቃድ ያስፈልጋታል::

ድረሻ በእናትነትና በሚስትነት ሲሆን ይህም በጣም የተቀደሰና አስፈላጊም ነው:: ልጆችን ምስቅልቅል ከሆነው ነፃ አዕምሯቸው አላቆ ብቁ ዜጋ እንዲሆኑ ለማድረግ የእናትን የአስተማሪነት ድርሻ የቤት ሰራተኞች ወይም ልጅ አሳዳጊዎች የማይችሉት ሃላፊነት ነው:: እንዲህ አይነቱ የተከበረና በጣም አስፈላጊ ድረሻ በአመዛኙ የወደፊቱን ትውልድ የሚለውጥና «ከስራ ፈትነት» ወይም ታፍኖ የመኖር ያህል አያስቆጥርም::

ሆኖም በእስልምና ህግ ውስጥ ሴትን አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ማለትም ከርሷ የተፈጥሮ ባህርይ ጋር የሚሄድና በዚያ የስራ መስክ ህብረተሰቡን የምታገለግል ከሆነ ስራ ለመፈለግ የሚያግዳት ድንጋጌ የለም:: ለምሳሌ የህክምና ሙያዎችን፣ አስታማሚ (ነርስ) መሆን፣ ማስተማርን /በተለይ ልጆችን/ ይሆናል:: ከዚህ በተጨማሪ በሴቶች ልዩ ችሎታ በሚንቀሳቀሱ የስራ መስኮች ከመስማራት የሚያግዳት የለም:: ምንም እንኳ ሴት ባላት ተፈጥሯዊ ስሜታዊነት ለብቁነቷ ጥርጣሬ ቢኖርም በዳኛነት ሙያ መሰማራ አቡሃኒፋና አጠበሪ ስህተት እንደሌለው ገልፀዋል::

ከዚህም በማያያዝ በአንዳንድ ባህሎች ራሷ እንደውርስ ዕቃ የምትታየው ሴት በእስልምና የመውረስ መብቷ

የተረጋገጠ ነው፡፡ የእርሷ ድርሻ የጠበቀና የግሏ ሲሆን ማንም ሊወስድባትና አባቷም ቢሆን ባሏ የግላቸው የማድረግ መብት የላቸውም፡፡

لِّلرِّجَالِ نَصِيبٌ مِّمَّا تَرَكَ ٱلْوَٰلِدَانِ وَٱلْأَقْرَبُونَ وَلِلنِّسَآءِ نَصِيبٌ مِّمَّا تَرَكَ ٱلْوَٰلِدَانِ وَٱلْأَقْرَبُونَ مِمَّا قَلَّ مِنْهُ أَوْ كَثُرَ ۚ نَصِيبًا مَّفْرُوضًا (٧)

«ለወንዶች ወላጆችና የቅርብ ዘመዶች ከተውት /ረጀት/ ፊንታ አላቸው፡፡ ለሴቶችም ወላጆችና የቅርብ ዘመዶች ከተውት ከርሱ ካነሰው ወይም ከበዛው ፊንታ አላቸው፡፡ የተወሰነ ድርሻ/ተደርጓል/፡፡» /4:7/

በአብዛኛው ሁኔታ የእርሷ ድርሻ የወንዱ ግማሽ ይሆናል፡፡ ይህም ሴት የወንድ ግማሽ ነች የሚል ግምት አያሳድርም፡፡ ከላይ ካየናቸው ተወዳዳሪ የሌላቸው የእስልምናን የሴት እኩልነት መብትን እንዲህ አይነት ግምት መስጠት የማይመስል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በእስልምና ህግ ውስጥ ያለው የሴትና ወንድ የውርስ መብት ልዩነትን የምናየው በቤት ውስጥ ባለው የማስተዳደር ሃላፊነት ልዩነት ብቻ ነው፡፡ በእስልምና ሃይማኖት ወንድ ሚስቱን፣ ልጆቹን፣ ችግረኛ ዘመዶቹን በተለይ ደግሞ ሴቶቹን በሙሉ የመንከባከብ ሃላፊነት አለበት፡፡ ይህንንም በእርሷ ሃብት ወይም በምታገኘው

ትርፍ ፣ ከኪራይ ገቢና በማንኛውም ህጋዊ መንገድ የምታገኘው ሃብት ሃላፊነቱን ሊለውጠው አይችልም።

በሌላ አንፃር የገንዘብ ሃላፊነትን በተመለከተ ነፃ ሲያደርጋት በንብረቷ ላይም የወጪ ጫና የለባትም። ንብረቷም ወደ ባሏ አይዛወርም። ስሟም አይቀየርም(እንደ ምዕራባዊያን ሴት በባሏ ቤተሰብ ስም አትጠራም)። ከጋብቻ በኋላ ለቤተሰቧ ከንብረቷ ወጪ ማድረግ ግዴታ ለባትም። በጋቻም ጊዜ በሚሰጣት «መኸር» ሃላፊዋ እርሷ ናት። ከተፈታችም ከቀድሞ ባሏ ክፍያ ይደረግላታል።

እስልምናን የውርስ ህግ መዋቅር በአጠቃላይ ስንገመግመው ፍትህን ብቻ ሳይሆን ግልፅ የሚያደርግልን ለሴት ከፍ ያለ ርህራሄ መኖሩንም ጭምር ነው።

## 4. የፓለቲካ ተሳትፎን በተመለከተ

የእስልምናን ትምህርቶች ወይም የእስልምናን ስልጣኔ በቅን መንፈስና አድልኦ በሌለበት ሁኔታ ጥናት ቢደረግ በእርግጥ የሴትን እኩልነት በተመለከተ ዛሬ ከምንጠራው «የፓለቲካ መብቶች» በበለጠ ግልፅ ማስረጃ እናገኛለን።

ይህም የሚያጠቃልለው በፓለቲካ ቢሮ ውስጥ የመመረጥና የመምረጥ መብት ነው። ይህም በህዝብ ጉዳዩች ላይ የሴት መብት እንዳለ ነው። በቁርዐንና በእስልምና ታሪክ ውስጥ ከነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) ጋር ውይይትና ክርክርም አድርገዋል።

قَدْ سَمِعَ ٱللَّهُ قَوْلَ ٱلَّتِى تُجَـٰدِلُكَ فِى زَوْجِهَا وَتَشْتَكِىٓ إِلَى ٱللَّهِ وَٱللَّهُ يَسْمَعُ تَحَاوُرَكُمَآ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ سَمِيعٌۢ بَصِيرٌ (١)

«አላህ በዚያች በባሏ /ነገር/ የምትከራከርህንና ወደ አላህ የምታሰሙተውን /ሴት/ ቃል በእርግጥ ሰማ። አላህም /በንግግር/ መመላለሳችሁን ይሰማል። አላህ ሰሚ ተመልካች ነውና.......» /58:1/

በከሊፋ ዑመር የአስተዳደር ዘመን አንድ ሴት መስጊድ መጥታ ስሞታዋን በስፋት ገልፃ ተከራከረቻቸው። እርሳቸውም በህዝብ ፊት፡- «ይህች ሴት ትክክል ናት ዑመር ስህተተኛ ነው» ብለዋል።

ምንም እንኳ በቁርዐን ባይጠቀስም አንድ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሃዲስ ሴት ለአገር መሪነት ብቁ እንደማትሆን ይገልፃል። ሃዲሱም ሲተረጉም የሚለው «ህዝቦች ሴትን

መሪ ካደረጉ አይበለፅጉም» የሚል ነው። ይህ ማዕቀብ ከርሷ ክብርና መብት ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም። ይህ የሚያሳየው በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለውን አካላዊና ስነ ልቦናዊ ልዩነት ነው።

በእስልምና መሪ የሚባለው  የአገር ፕሬዘንዳት ብቻ ሳይሆን ሶላትን በኢማምነት በተለይ በዐርብና የባዕላት ቀን  የሚያሰግድ፤ የሚመራውን ህዝብ ፀጥታውንና ደህንነቱን በተመለከተ ሁሌ ውሳኔ መስጠት መቻል አለበት። ከዚህም በላይ በጦር መሪነትም የሚያገለግልና በአጠቃላይም ሴት ካላት አካላዊና ስነልቦናዊ አፈጣጠር ጋር የማይሄድ መሆኑ ነው። በህክምና  እንደተረጋገጠው ሴቶች በወር አበባቸውና በእርግዝናቸው ወቅት የተለያዩ አካላዊና ስነልቦናዊ ለውጦች ይፈራረቁባቸዋል።

ይህ አይነቱም ለውጥ በአስቸኳይ ሁኔታዎች ላይ ሊያጋጥሙ ይችላሉ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ጭንቀትና መጠበብን ስለሚያስከትል በሚሰጡት ውሳኔ ላይ ችግር ይፈጥርባቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ አንዳንድ ውሳኔዎች ከፍተኛ ማስተዋልንና አነስተኛ ስሜታዊነትን ይሻሉ። በዚህ ረገድ ሴቶች ካላቸው ተፈጥሯዊ ፀባይ ጋር የሚሄድ አይሆንም።

በአሁኑ ዘመን እንኳን በጣም በሰለጠኑ አገሮች በአገር መሪነት፣ በጦር መሪነት በፓርላማ ውስጥ እንኳን ያላቸው ወንበር ወይም በተመሳሳይ ድርጅቶች ውስጥ ያላቸው ድርሻ ውሱን ነው:: በህገ መንግሥት ድንጋጌ ላይ የሴቶችን መብት በመግፈፍ መሪ ያለመሆን ወይም ደግሞ በህግ መወሰኛ ምክር ቤት ውስጥ አባል ያለመሆንና እንዲህ ያለውን አመራር የማያራምዱ አገሮች ኋላ ቀር አያሰኛቸውም::

በትክክል ሁኔታዎችን ብንመለከት የማያሻማ ተፈጥሯዊ ልዩነት አለ ማለትንና ይህም አንዱ በሌላው ላይ «የበላይነት» የሌለው መሆኑን ነው:: ልዩነቱ የሚያሳየው የሁለቱም ፆታዎች በህይወት ውስጥ «ተደጋጋፊ» ድርሻ እንዳላቸው ነው::

## ማጠቃለያ

የመጀመሪያው የዚህ ጥናት ፅሁፍ ያተኮረው በተለያዩ ሃይማኖቶችና ባህሎች ላይ የተደረገ ጥናት ነው:: ከዚያም ከ1300 ዓመት በኋላ የነበረውን የእስልምና ትምህርት እስከ አስራ ዘጠኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያ አካባቢ ያለውን የሴቶች ማዕረግ በስፋት ለመግለፅ ተሞክሯል::

በሁለተኛው ክፍል በእስልምና ውስጥ ያለው የሴቶች ማዕረግ በአጭሩ ተገልጿል:: ይህም የሚያሳየው ሙስሊሞች ፍርድ በመስጠት በኩል ምን ያህል ታማኝ መሆናቸውን ያሳያል::

በሌላ በኩል ደግሞ የእስልምና ስልጣኔ ወደኋላ በተጎተተበት ሰዓት እስልምናን በተቀበሉ ተከታዮች እነዚህ መመሪያዎች ጥቅም ላይ እንዳልዋሉ ያሳያል:: ይህ ወደ ኋላ የማፈግፈግ ሁኔታ በአንዳንድ ፀሃፊዎች ሲጋነንና በምዕራባዊያን አንባቢያን ዘንድ በማያዳላ

ሁኔታና ጥልቅ ጥናት ሳያደርጉ የእስልምና ትምህርቶችን በጥራዝነጠቅ ሲያዩ ተስተውለዋል።

በዚህም ላይ ሶስት እውነታዎችን መጥቀስ አስፈላጊ ይሆናል፡-

1. በእስልምና ታሪክ ውስጥ በሁሉም የኑሮ መስክ ሴቶች እስከ ሰባተኛው ክፍል ዘመን መጨረሻ ድረስ ከፍተኛ ክንውኖችን አሳይተዋል።

2. ማንም ሰው በእስልምና ህግ ውስጥ ሴትን የሚጨቁን ህግ ተደንግጓል ማለት ወይም ደፍሮ ህግን ማጥፍትና መቀነስ ወይም በእስልምና የደነገገውን ትክክለኛ መብት ማዛባት አይችልም።

3. በታሪክም ውስጥ የሙስሊም ሴቶች ዝና፣ ክብርና የእናትነት ድርሻ በማያዳሉ ታዛቢዎች ዘንድ የሚደነቁ ምሳሌዎች ነበሩ።

እዚህ ላይ በተጨማሪ መጠቀስ ያለበት በአሁን ወቅት ሴቶች የተቀዳጁት መብት የመጣው በወንዶች ርህራሄ ወይም በተራማጅነት ስሜት አይደለም። ይህንን መብት የተቀዳጁት በረዥም ጊዜ ትግልና በተለይ ከሁለቱ የአለም ጦርነቶች

ወዲህ የታየው የቴክኖሎጂ እድገትና ህብረተሰቡ በስራ እንዲካፈሉ ስለፈለገ ብቻ ነው።

እስልምናን በተመለከተ እዝነትና ክብርን የሚያጎናፅፍ ህግጋት ተደንግገዋል። ይህም የሰባተኛውን ክፍለ ዘመን ሁኔታ ብቻ ሳይሆን የሚያፀባርቀው የህግጋቱን እውነተኛነት ነው።

ይህ የሚያሳየው የቁርዐንን አምላካዊ ድንጋጌ መሆኑንና በእርግጥ የእስልምና ተአምር መሆኑን ነው። ይህም ከሰው ልጆች ፍልስፍናዎችና ርዕዮተ አለሞች ጋር የማይገናኝና ያለፈውም ህብረተሰብ በሰብአዊ መመርያነት የሰራበትና አሁንም ያለው ህብረተሰብ ፣ የሚቀጥለውም ህብረተሰብ የሚሰራበት መሆኑን ነው።

ከሁሉም በበለጠ ይህ መልዕክት የጥበበኛው፣ የአዋቂው፣ ጥበቡና እውቀቱ ከሰው አመለካከትና ዕድገት በጣም የራቀ ከሆነው አላህ(ሱብሃነሁ ወተዓላ) ነው።